የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፴፭
አዲስ አበባ–ጥር ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፭

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

9th Year No. 35
ADDIS ABABA–6th February, 2003


## ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፫፻፲፯/፲፱፻፺፭ ዓ·ም

የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ፈንድ ማቋቋሚያ አዋጅ ...................... ገጽ ፪ሺ፺፰


## CONTENTS


Proclamation No. 317/2003

Rural Electrification Fund Establishment Proclamation ...................... Page 2098


## አዋጅ ቁጥር ፫፻፲፯/፲፱፻፺፭

## የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ፈንድ ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

የገጠሩን አካባቢ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ለማሻሻል የኤሌክትሪክ አገልግሎት ማቅረብ አስፈላጊ በመሆኑ፣

በብድር ላይ የተመሠረተ የቴክኒክ አገልግሎትና የፋይናንስ ድጋፍ በመሥጠት በገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ተግባር የሚሠማሩ የግል ባለሀብቶችን እና የኅብረት ሥራ ማህበራትን ማበረታታት አስፈላጊ በመሆኑ፣

ለዚህ ተግባራዊነት የፋይናንስ ምንጭ ሆኖ የሚያገለግል ፈንድ ማቋቋም አስፈላጊ በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ፈንድ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፫፻፲፯/፲፱፻፺፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጥ ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

፩· "ኤጀንሲ" ማለት የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኤጀንሲ ነው፣

## PROCLAMATION NO. 317/2003

## A PROCLAMATION PROVIDED FOR THE ESTABLISHMENT OF THE RURAL ELECTRIFICATION FUND

WHEREAS, it is necessary to provide electricity service to improve economic and social development of rural areas;

WHEREAS, it is necessary to promote private and cooperative engagement in rural electrification activities through loan based finance and technical services;

WHEREAS, to achieve this it is important to establish a fund to serve as a source of finance;

NOW, THEREFORE, in accordance with Aricle 55 (1) of the Constitution of the Federal Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

### PART ONE
### *General*

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Rural Electrification Fund Establishment Proclamation No. 317/2003."

2. *Definitions*

Unless the context otherwise requires, in this Proclamation:

1) "Agency" means the Ethiopian Electricity Agency;

፪· "ማዕከል" ማለት በአዋጅ ቁጥር ፪፻፷፱/፲፱፻፺፬ የተቋቋመው የኢትዮጵያ የገጠር ኢነርጂ ልማትና ማስፋፊያ ማዕከል ነው፤

፫· "ኮርፖሬሽን" ማለት የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን ነው፤

፬· "ዳይሬክተር" ማለት የኢትዮጵያ የገጠር ኢነርጂ ልማትና ማስፋፊያ ማዕከል ዋና ዳይሬክተር ነው፤

፭· "አስፈጻሚ ሴክሬታሪያት" ማለት የኢትዮጵያ የገጠር ኢነርጂ ልማትና ማስፋፊያ ማዕከል ነው፤

፮· "ከግሪድ ውጭ" ማለት በኮርፖሬሽን ያልተሸፈነ የኤሌክትሪክ አቅርቦት ነው፤

፯· "የገጠር አካባቢ" ማለት ከግሪድ ውጭ ያለ አካባቢ ነው፤

፰· "መንግሥት" ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ነው፤

፱· "ሚኒስቴር" እና "ሚኒስትር" ማለት እንደ ቅደም ተከተላቸው የገጠር ልማት ሚኒስቴር እና ሚኒስትር ነው፤

፲· "ኦፐሬተር" ማለት ከግሪድ ውጭ ለንግድ ዓላማ ኤሌክትሪክ የማመንጨት፣ የማከፋፈልና የመሸጥ ሥራ የሚሠራ ሰው ነው፤

፲፩· "ኦፐሬሽን" ማለት ከግሪድ ውጭ ለንግድ ዓላማ ኤሌክትሪክ የማመንጨት፣ የማከፋፈልና የመሸጥ ሥራ ነው፤

፲፪· "የገንዘብ ባለአደራ ተቋም" ማለት ከፈንዱ ልዩ ልዩ ምንጮች የሚሰበሰበውን ገንዘብ የሚያስቀምጥና በቦርዱ ትዕዛዝ ብድር የሚሰጥና ብድሩንም ተቀብሎ በፈንዱ የባንክ ሂሳብ የሚያስቀምጥ ማንኛውም የፋይናንስ ተቋም ነው፤

፲፫· "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፵፯/፩/ የተገለጸ ክልል ሲሆን፤ ለዚህ አዋጅ ዓላማ አፈጻጸም አዲስ አበባና ድሬዳዋን ይጨምራል፤

፲፬· "ታዳሽ የኃይል ምንጭ" ማለት ከተፈጥሮ የሚገኝ በራሱ ወይም በሰው አማካይነት በማያቋርጥ ዑደት ሂደቱን ጠብቆና እንደአስፈላጊነቱ ተተኪም በመሆን ለሰዎች አገልግሎት ጥቅም ላይ የሚውል እንደ የፀሐይ፣ የነፋስ፣ የውሃ፣ የባዮማስና የመሳሰሉት የኃይል ምንጭ ነው፤

፲፭ "የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን" ማለት ከግሪድ ውጭ ኤሌክትሪክ ማመንጨት፣ ማስተላለፍ፣ ማከፋፈል፣ መሸጥና እነዚህን ለማስፈጸምና ለማስፋፋት የሚከናወኑ ተጓዳኝ ተግባሮች ናቸው፤

፲፮ "የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን መርሐ-ግብር" ማለት በገጠር አካባቢ ለፈንዱ ከተቀመጡት ዓላማዎች አንፃር በፈንዱ እየታገዘ የኤሌክትሪክ አቅርቦትን ለማስፋፋት በቦርዱ የሚጸድቅ የእንቅስቃሴ አቅጣጫ ነው፤

፲፯ "የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ፕሮጀክት" ማለት ከግሪድ ውጭ የኤሌክትሪክ አገልግሎትን ለማዳረስ የሚከናወን የዲዛይን፣ የግንባታ፣ የማመንጨት፣ የማስተላለፍና ሌሎች ተጓዳኝ ሥራዎች ናቸው፤

፲፰ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፲፱ "የአሠራር ወጥነት መመሪያ" ማለት በፈንዱ ልዩ ልዩ አካላትና ፈንዱን በሚያስፈጽሙ የክልል አስፈጻሚ ጽሕፈት ቤቶች የሚከናወኑ የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ተግባራት ወጥነትና ቅንጅት ባለው አኳኋን እንዲሠሩ የሚመራ መመሪያ ነው።

፫· መቋቋም

የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ፈንድ (ከዚህ በኋላ "ፈንዱ" እየተባለ የሚጠራው) ቋሚ የፋይናንስ ምንጭ ሆኖ የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚከፍተው ልዩ የባንክ ሂሳብ ውስጥ ተቀማጭ እንዲሆን በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

2) "Center" means the Ethiopian Energy Development and Promotion Center established by Proclamation No. 269/2002;

3) "Corporation" means the Ethiopian Electric Power Corporation;

4) "Director" means the Director General of the Ethiopian Development and Promotion Center;

5) "Executive Secretariat" means the Ethiopian Rural Energy Development and Promotion Center;

6) "Off-grid" means any electric supply not covered by the Ethiopian Electric Power Corporation Electric Supply System;

7) "Rural Area" means any off-grid area;

8) "Govermment" means the Govermment of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;

9) "Ministry" and "Minister" means the Ministry and Minister of Rural Development respectively;

10) "Operator" means a person who generates, distributes, and sells electricity in off-grid areas for commercial purpose;

11) "Operation" means the activity of generating, distributing and selling in off-grid areas for commercial purposes;

12) "Trust Agent" means any financial institution that keeps the money collected from various sources of the fund as well as renders and collects loan upon the order of the Board;

13) "Region" means a region designated by Article 47 (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and, for the purpose of this Proclamation, includes the Addis Ababa and Dire Dawa Administrations;

14) "Renewable Energy Source" means an energy source of nature such as solar, wind, hydro, biomass and the like, which naturally recycles or recycled by man-induced processes useful to man.

15) "Rural Electrification" means all activities of generation, transmission, distribution and other related activities of electricity in off-grid areas;

16) "Rural Electrification Program" means an activity direction approved by the Board that promotes electricity supply in rural areas with the support by the Fund and in respect to the objectives of the Fund;

17) "Rural Electrification Project" means a single activity of designing, constructing, generating, transmitting, and performing other related activeties to achieve the distribution of electricity in rural off-grid areas;

18) "Person" means a natural or juridical person;

19) "Uniformity Directive" means a directive issued to maintain co-herence and co-ordination in the activities of various units of the Fund and regional implementing offices.

3. *Establishment*

The Rural Electrification Fund (hereinafter 'the Fund") is hereby established by this Proclamation as a permanent financial source to be deposited under Special Bank Account to be opened by the Ministry of Finance and Economic Development.

**፬· የፈንዱ ዓላማዎች**

ፈንዱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፣

፩· በግል ፣ በህብረት ሥራ ማህበራትና በአካባቢ ኅብረተሰብ ለሚከሄዱና በተለይም በዋነኝነት ታዳሽ የኃይል ምንጮችን ለሚጠቀሙ የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ፕሮጀክቶች የብድርና የቴክኒክ አገልግሎት መስጠት፣

፪· በገጠሩ አካባቢ የኤሌክትሪክ አገልግሎት ለምርትና ለማህበራዊ አገልግሎት እንዲውል ማበረታታት።

**፭· የፈንዱ ምንጮች**

የፈንዱ ምንጮች የሚከተሉት ይሆናሉ፣

፩· ከመንግሥት የሚመደብ በጀት፣

፪· ከሌሎች መንግሥታት የሚገኝ ብድርና ዕርዳታ፣

፫· ከዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅቶች የሚገኝ ብድርና ዕርዳታ፣

፬· መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ከሚገኝ ዕርዳታ፣

፭· ከሌሎች ልዩ ልዩ ምንጮች የሚገኝ ገቢ።

## ክፍል ሁለት
## የፌዴራል የፈንዱ አካላት

**፮· የፈንዱ አካላት**

፩· ፈንዱ በፌዴራል ደረጃ፣

ሀ) በገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ቦርድ (ከዚህ በኋላ "ቦርዱ" እየተባለ የሚጠራ)፣

ለ) አስፈጻሚ ሴክሬታሪያት፣

ይኖረዋል

፪· ቦርዱ ተጠሪነቱ ለሚኒስትሩ ይሆናል፣

፫· ክልሎች የራሳቸውን የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን አስፈጻሚ ሴክሬታሪያት ሊያቋቁሙ ይችላሉ፣

፬· የክልል የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ሴክሬታሪያት ጽሕፈት ቤቶች፣ የየክልሎቻቸው የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ፕሮጀክቶች በዚህ ሕግና ቦርዱ በሚያወጣቸው ልዩ ልዩ መርሐ-ግብሮችና መመሪያዎች መሠረት መከናወናቸውን ይከታተላሉ።

**፯· የቦርዱ አባላት**

፩· ቦርዱ በመንግሥት የሚሰየሙ አባላት ይኖሩታል።

፪· የቦርዱ አባላት የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል። ሆኖም ማንኛውም አባል ለተጨማሪ የሥራ ዘመናት እንደገና ሊመደብ ይችላል።

፫· አንድን የቦርድ አባል መንግሥት በማናቸውም ጊዜ እና ምክንያት ሊያነሳው እና በሌላ ሊተካው ይችላል።

፬· የቦርዱ አባላት ቁጥር በሞት፣ ሥራን በፈቃድ በመልቀቅ ወይም በማናቸውም ሌላ ምክንያት ቢቀንስ፣ ክፍት ቦታው በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ይሞላል።

፭· ማንኛውም የቦርድ አባል በቦርዱ ውስጥ ካለው ሥራ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በጥቅም የሚጋጭ ማንኛውንም ተግባር ማከናወን የለበትም። በቦርዱ ውስጥ ካለ ሥራ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የጥቅም ግጭት ሲያጋጥመው ይህንኑ ለቦርዱ በማሳወቅ ጉዳዩ ከሚታይባቸው የቦርዱ ስብሰባዎች እራሱን ማግለል አለበት።

**፰· የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር**

ቦርዱ የሚከተሉት ተግባራት ይኖሩታል፣

፩· ሚኒስቴሩን በፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ያማክራል፣

፪· የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን መርሐ-ግብርን ሥራ ላይ ለማዋል የሚያገለግሉ የአሠራር ሥርዓቶችን፣ መመሪያዎችን ፣ ደረጃዎችንና የፕሮጀክት አፈጻጸም መመሪያዎችን ያፀድቃል። እነዚህኑ በየጊዜው እየመረመረ ተገቢውን ማስተካከያ ያደርጋል፣

4. *Objectives of the Fund*

The Fund has the followig objectives:

1) To provide loan and technical services for Rural Electrification Projects carried out by private operators, cooperatives and local communities and more specifically for those projects operating on renewable energy sources;
2) To encourage the utilization of electricity for production and social welfare purposes in rural areas.

5. *Sources of Fund*

The sources of the Fund shall be:

1) Budget allocated by the Government;
2) Loans and grants from other Governments;
3) Loans and grants from International Financial Institutions;
4) Grants from non-Governmental Organizations;
5) Income from other different sources.

## PART TWO
## *Federal Organs of the Fund*

6. *Organs of the Fund*

1) At the Federal level, the Fund shall have:
   (a) Rural Electrification Board (hereinafter "the Board")
   (b) an Executive Secretariat.
2) The Board shall be accountable to the Minister.
3) Regional Governments may establish their own Rural Electrification implementing Secretariats.
4) Regional Rural Electrification implementing Secretariats shall follow up and confirm whether the projects in their respective Regions are implemented in conformity with this Proclamation, and programmes and the directives issued by the Board.

7. *Members of the Board*

1) The Board shall have members to be designated by the Government.
2) The term of office of any member of the Board shall be five years, provided, however, that he may be re-assinged for additional terms of office by the organ, which nominates him.
3) The organ, which has assigned a member of the Board, may at any time and for any reason recall and replace him by another.
4) In case of reduction in the number of Board members due to death or resignation of a member or due to any other reason, the vacant post shall be filled within three months.
5) Any member of the Board shall not engage in any activity that may be directly or indirectly conflicting with his capacity as a Board member. When the member encounters a conflict of interest, he shall disclose such conflict to the Board and withdraw from all meetings of the Board at which such matters are discussed.

8. *Powers and Duties of the Board*

The Board shall have the following powers and duties:

1) Advise policy issues to the Ministry;
2) Approve directives, working procedures, standards and project implementation guidelines that serve to implement rural electrification programs;

፫· ብድር ለመስጠት የሚያስችሉ ግልፅ መመሪያዎች፣ መስፈርቶችና አግባብ ያላቸውን የአሠራር ሥርዓቶች ያፀድቃል፣

፬· በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፮ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት አገልግሎታቸውን በኮርፖሬሽኑ አማካይነት ለለቀቁ ኦፕሬተሮች ካሳ የሚከፈልበትን መስፈርት አውጥቶ በሚኒስቴሩ ያስፀድቃል፣

፭· ሪፖርቶችን ይቀበላል፣ ይመረምራል፣ እንደ አስፈላጊነታቸው ያፀድቃል፣

፮· ፈንዱን ያስተዳድራል፣

፯· ከልዩ ልዩ የፈንዱ ምንጮች ገቢ የሚደረገውን ገንዘብ በኃላፊነት የሚያስቀምጥ የገንዘብ ባለአደራ ተቋም በሴክሬታሪያቱ ሲቀርብለት ያጸድቃል፣

፰· ስለ ገንዘብ ባለአደራ ተቋሙ ዝርዝር አሠራር መመሪያ ያወጣል፣

፱· አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሥልጣንና ተግባሩን ለክልል የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ሴክሬታሪያት ጽሕፈት ቤቶች በውክልና ሊሠጥ ይችላል፣

፲· የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽንን የሚያጠናክሩ ሌሎች ሥራዎች ያከናውናል፣

፲፩· የቦርዱ ውሳኔዎች፣ መርሐግብሮች እና አመራሮች ለሕዝብ ግልፅ እንዲሆኑ ያደርጋል፣

፲፪· በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ ከተጠቀሱት የፈንዱ ምንጮች የሚገኘው ገቢ በሚመለከተው አካል በጊዜው መሰብሰቡን ያረጋግጣል።

፱· የቦርዱ ስብሰባዎች

፩· ቦርዱ በየሦስት ወሩ ይሰበሰባል። ሊቀመንበሩ ሲጠራ በማናቸውም ጊዜ ሌሎች አስቸኳይ ስብሰባዎችን ያደርጋል።

፪· ከቦርዱ አባላት ከግማሽ በላይ በስብሰባው ላይ ከተገኙ ምልዐተ ጉባኤ ይሆናል።

፫· የቦርዱ ውሳኔ ሆኖ የሚፀናው በስብሰባው ከተገኙት ከግማሽ በላይ ድምፅ የሰጡበት ውሳኔ ነው። እኩል ድምፅ ሲገኝ ሊቀመንበሩ ድምፁን የሰጠበት ወገን አብላጫ ድምፅ ይሆናል።

፬· ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

፲· የአስፈጻሚ ሴክሬታሪያቱ ሥልጣንና ተግባር

አስፈጻሚ ሴክሬታሪያቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፣

፩· ዓመታዊና አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ሪፖርትን በማዘጋጀት በቦርዱ ያስፀድቃል፣

፪· የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ፕሮጀክት አፕሬተሮችን ማመልከቻ ይመረምራል፣ ቦርዱ ባፀደቃቸው መስፈርቶች መሠረት ይወስናል፣

፫· መስፈርቶችን አውጥቶ በውድድር ላይ በተመሠረተ አሠራር ባለአደራ የፋይናንስ ተቋምን ይመርጣል፣ ይህንኑ እንዲያፀድቀው ለቦርዱ ያቀርባል፣

፬· ብድር የሚሰጥባቸውን ግልፅ መመሪያዎችና አግባብ ያለውን የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ፕሮጀክት ለመምረጥ የሚያስችሉ የምርጫ መስፈርቶችና ሥርዓቶችን አዘጋጅቶ ለቦርዱ በማቅረብ ያስፀድቃል፣

፭· የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን መርሐ-ግብር ከሌሎች የገጠር ልማት ተግባራት ጋር እንዲቀናጅ የበኩሉን አስተዋጽኦ ያደርጋል፣

፮· በገጠር ውስጥ የኤሌክትሪክ አገልግሎት እንዲስፋፋ፣ ለምርትና ማህበራዊ ጥቅም እንዲውል ያደርጋል፣

፯· የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ጣቢያዎችን ለመትከል፣ ለማንቀሳቀስና ለማስተዳደር በሚያስችሉ የአቅም ግንባታ ተግባሮች ላይ ከሚመለከታቸው ጋር ይተባበራል፣

3) Approve transparent directives, criteria and appropriate working procedures that enable the issuance of loans;

4) Set–out compensation criteria to be approved by the Ministry, for those operators whose operations are taken over by the Corporation as specified in Article 16 (4) of this Proclamation;

5) Receive, and examine reports and approve same when appropriate;

6) Administer the Fund;

7) Approve the nomination of a Trust Agent that shall be entrusted with the Fund to be secured from different sources, as presented to it by the Executive Secretariat;

8) Issue detailed directives for the Trust Agent;

9) Delegate, when it deems appropriate, its powers and duties to Regional Rural Electrification Secretariat Office;

10) Engage in other activities that enhance rural electrification;

11) Maintain transparency to the public regarding its decisions, program and leadership;

12) Ensure timely collection of the fund, by the relevant body, from the different sources specified in Article 5 of this Proclamation.

9. *Meetings of the Board*

1) The Board shall have meetings every three months. Extraordinary meetings may be held at any time when called by the chairperson.

2) There shall be a quorum where more than half of the members of the Board are present at a meeting.

3) Decisons of the Board shall be made valid if more than half of those present voted in favor. In the event of a tie, the chairperson shall have a casting vote.

4) The Board may adopt its own rule of procedures with regard to its meetings.

10. *Powers and Duties of the Executive Secretariat*

The Executive Secretariat shall have the following powers and duties:

1) prepare annual, and whenever required, report and submit it for the approval of the Board;

2) review applications from rural electrification project sponsors and based on the criteria approved by the Board decide on the applications;

3) set out criteria for the competitive selection of a Trust Agent and submits same to the Board for approval;

4) prepare and submit to the Board, for approval, transparent directives and selection criteria and procedures to be used in the issuance of loans and identification of appropriate rural electrification project;

5) facilitate and submit the co-ordination of the rural electrification program activities with other rural development activities;

6) promote and support access to and productive use of electricity in the Rural area;

7) cooperate with relevant bodies for capacity building regarding Rural electrification project installation, operation and Management;

፰· ተቀባይነት ያላቸውንና የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን የደህንነት ደረጃና ኢኮኖሚያዊ አቅም ያገናዘቡ ቁሳቁሶችን፣ መሣሪያዎችንና ቴክኖሎጂን ዝርዝር ያዘጋጃል፣ ይይዛል። እንዲሁም በመረጃነት እንዲሠራጩ ያደርጋል፣

፱· ለፈንዱ ተጨማሪ የገቢ ምንጭ ሊሆኑ የሚችሉ ሁኔታዎችን ያጠናል፣

፲· የቦርዱን የሥራ መዛግብት፣ ዘገባዎችና የስብሰባ ቃለ ጉባኤዎች ይይዛል፣ እንዲሁም የቦርዱ ውሳኔዎችና መመሪያዎች በትክክል መፈጸማቸውን ተከታትሎ ያረጋግጣል፣

፲፩· በዚህ አዋጅ ከተጠቀሱት የፈንዱ ምንጮች የሚገኘው ገንዘብ በጊዜው መሰብሰቡንና በፈንዱ ሂሳብ ገቢ መደረጉን ያረጋግጣል፣

፲፪· ሌሎች ከተግባርና ኃላፊነቱ ጋር የሚገናኙ ሥራዎችን ይሠራል፣

፲፫· ፈንዱ በየጊዜው ለሚወጠነው የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ፕሮግራም የበለጠ ውጤታማ በሆነ መንገድ ሥራ ላይ የሚውልበትን እያጠና ለቦርዱ የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል።

**፲፩· የዲሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር**

ዲሬክተሩ ፈንዱን በሚመለከቱ ጉዳዮች ተጠሪነቱ ለቦርዱ ሆኖ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲ የተመለከቱትን የአስፈጻሚ ሴክሬታሪያቱን ሥልጣንና ተግባሮች በሥራ ላይ ያውላል።

## ክፍል ሦስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፲፪· የአሠራር ወጥነት**

፩· የአሠራር ወጥነት እንዲኖር ሁሉም የፈንዱ አሠራሮችና ተግባሮች በአሠራር መመሪያ ይመራሉ።

፪· ቦርዱ የአሠራር መመሪያ ያወጣል።

**፲፫· የገንዘብ ባለአደራው ተቋም ኃላፊነት**

፩· የገንዘብ ባለአደራው ተቋም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ ከተጠቀሱት የፈንዱ ምንጮች የሚገኘውን ገንዘብ በኃላፊነት ይይዛል።

፪· በቦርዱ ትዕዛዝ ለገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ፕሮጀክቶች የሚሰጠውን ብድር ይሰጣል፣ በብድር የተሰጠ ገንዘብ ሲመለስ ይቀበላል።

፫· ተበዳሪዎች የወሰዱት ገንዘብ በጊዜው መመለሱን ይከታተላል።

፬· የፈንዱን ገቢና ወጪ የሚያሳይ የሂሳብ መዝገብ ያዘጋጃል። ይህንኑ ቦርዱ በመመሪያ በሚወስነው ጊዜ ለቦርዱ ያቀርባል።

፭· ሌሎች ከኃላፊነቱ ጋር አግባብ ያላቸውን ሥራዎች ይሠራል።

**፲፬· ለገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ፕሮጀክቶች ፈቃድ ስለመስጠት**

ኤጀንሲው አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ለገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ፕሮጀክቶች ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ያቋርጣል፣ ይሰርዛል።

**፲፭· ለብድር ብቁ ስለመሆን**

ከፈንዱ ለመበደር የሚፈልግ ሰው በገጠር ኤሌክትሪክሽን ሥራ ለመሠማራት ብቁ መሆንና ብድር ለማግኘት የሚያስችሉ መስፈርቶችን ማሟላት አለበት።

**፲፮· የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን አልሚዎች ዋስትና**

፩· የኮርፖሬሽኑ የኤሌክትሪክ አቅርቦት በየ፲ ዓመት ምን ያህል የአገሪቱን ክፍል እንደሚሸፍን የሚያሳይ ጠቋሚ የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ማስተር ፕላን ማውጣት አለበት።

8) prepare, maintain, issue and disseminate equipment, devices and appliances that meet acceptable safety standards and economy for rural electrification;
9) study additional ways and sources of finance to be used for the Fund;
10) compile and keep the working papers, reports and minutes of the Board, further it follows up and confirm the appropriate implementation of the directives of the Board and its decisions;
11) follow up and ensure the timely collection and deposit of the money from the sources specified in this Proclamation in the account of the Fund;
12) perform such other activities related to its powers and duties;
13) make recommendations to the Board regarding the most effective use of the Fund for the rural electrification program as set out from time to time.

11. *Powes and Duties of the Director*

The Director shall put into practice all the powers and duties of the Executive Secretariat as stated under Article 10 of this Proclamation, and shall be accountable to the Board with regard to the Fund.

## *PART THREE*
## *Miscellaneous Provisions*

12. *Uniformity of Practice*
1) With a view to ensuring uniformity of practice, the Operational Directive shall govern all operations and activities of the Fund.
2) The Board shall issue Operational Directive.

13. *Responsibility of the Trust Agent*
1) The Trust Agent shall be responsible for the administration of income accrued from various sources of Fund provided in Article 5 of this Proclamation.
2) It shall disburse loans for rural electrification projects upon the order of the Board; and shall collect reimbursement of loans.
3) It shall follow up periodic reimbursement of loans by borrowers.
4) It shall prepare financial document revealing the revenues and expenditure of the Fund; and shall, upon directives to be issued by the Board, submit to the same.
5) It shall carry out other activities pertaining to its responsiblity.

14. *Licensing of Rural Electrificaiton Projects*

The Agency shall apply relevant law to issue, renew terminate and revoke licenses for rural electrification porject.

15. *Eligibility for Loan*

A person who is interested to engage in rural electrification activities, shall be eligible for loan financing, provided, however, that he is a legal person and fulfils the criteria required for such financing.

16. *Protection to Rural Electrification Operators*
1) The Corporation shall issue or cause to be issued every 10 years and indicative national rural electrification master plan showing the expansion of the national grid covering the whole country.

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሰው የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ማስተር ፕላን ለሕዝብ ግልፅና የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽንን ፕሮግራም በማስፈጸም ረገድ ተገቢ ትኩረት የሚሰጠው መሆን አለበት።

፫· ኮርፖሬሽኑና ሴክሬታሪያቱ በየዓመቱ እየተገናኙ ለሚኒስቴሩና ለኤጀንሲው ከሚያቀርቡት ዓመታዊ የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ጠቋሚ ዕቅድ አኳያ ዕቅዳቸውን ያቀናጃሉ።

፬· የኮርፖሬሽኑ ኤሌክትሪክ አቅርቦት ሂደት በገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ተግባር የተሠማራውን ባለሀብት፣ የኀብረት ሥራ ማህበር ወይም የአካባቢ ኀብረተሰብ ያስለቀቀ እንደሆነ ለአልሚው ፈጣንና ትክክለኛ ካሣ ይከፈለዋል።

## ፲፯ የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ደንበኞች መብት

፩· ኦፕሬተሩ ኤጀንሲው በሕግ በተሰጠው ሥልጣን አማካይነት ከሚወስነው ኤሌክትሪክ ታሪፍ በላይ አያስከፍልም።

፪· የኤሌክትሪክ አገልግሎቱን ከማቋረጡ በፊት ኦፕሬተሩ አግባብ ባለው መንገድ ለደንበኛው ማሳወቅ አለበት።

፫· ኦፕሬተሩ የኤሌክትሪክ አገልግሎቱን ከማቆሙ ከ፫ ወር በፊት ለኤጀንሲው ማሳወቅ አለበት።

፬· አግባብ ባለው ሕግ ስለ ኤሌክትሪክ ደንበኞች መብት የተደነገጉት ድንጋጌዎች፣ ለገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ደንበኞችም ተፈጻሚ ይሆናል።

## ፲፰· ከብሔራዊ ግሪድ ጋር መያያዝ

አስፈጻሚ ሴክሬታሪያቱ የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ፕሮጀክቶች ወደፊት ከብሔራዊ ግሪድ ጋር በሚገናኙበት አቅጣጫ እንዲንቀሳቀሱ ፕላን ያወጣል ፣ ይህንኑ ይመክራል።

## ፲፱· የፀደቁ ፕሮጀክቶች ቁጥጥርና ክትትል

የአስፈጻሚ ሴክሬታሪያቱ እንደአስፈላጊነቱ የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ፕሮጀክቶች ለፕሮጀክቶቹ ክንዋኔ በፀደቀው መርሐ ግብር መሠረት መከናወናቸውን ይቆጣጠራል፣ ያረጋግጣል ፣ ለፕሮጀክቱ በተገባው ውል መሠረትም አስፈላጊውን ሕጋዊ እርምጃ ይወስዳል።

## ፳· የመንገድና የመሬት አጠቃቀም

የኤሌክትሪክ አዋጅ ቁጥር ፹፮/፲፱፻፹፱ ስለ መንገድና መሬት አጠቃቀም የሚደነግገው ለገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ፕሮጀክቶችም ተፈጻሚ ይሆናል።

## ፳፩· የአካባቢ ጥበቃ

የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ፕሮጀክቶች ዕቅድ፣ ግንባታ፣ ሥራና ጥገና የአካባቢ ጥበቃ ሕጎችን ያከበሩ መሆን አለባቸው።

## ፳፪· ደህንነት

፩· ኦፕሬተሮች ሠራተኞቻቸውን፣ ሕዝቡንና ንብረቱን ከአደጋ ለመጠበቅ ተገቢ የሆነውን ቅድመ ደህንነት እርምጃ ይወስዳሉ።

፪· የኤሌክትሪክ አዋጅ ቁጥር ፹፮/፲፱፻፹፱፣ ደንብ ቁጥር ፵፱/፲፱፻፺፩ እና የደህንነት መመሪያዎች በገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ።

## ፳፫· የሂሣብ መዛግብት

አስፈጻሚ ሴክሬታሪያቱ የፈንዱን ትክክለኛና የተሟሉ የሂሣብ መዛግብትና አስረጅ ሰነዶችን ይይዛል።

2) The rural electrification master plan specified in Sub-Article (1) of this Article shall be made open to the public and due attention shall be given to it in implementing rural electrification project.

3) The Corporation and the Secretariat shall meet each year to delineate their plan in light of the annual indicative national rural electrification plans they shall submit to the Minister and the Agnecy.

4) In the event that power supply activity of a rural electrification operation is taken over by expansion of the Corporation's activity, the owner of the rural electrification operation shall be provided with prompt, fair and adequate compensation as set out in the criteria.

## 17. *Protection of Rual Electrification Customers*

1) The Operator shall not charge in excess of the electricity tariff pursuant to the law that causes the Agency to set out tariffs.

2) The Operator shall issue prior notice to the customer by an appropriate means where there shall be serivce interruption.

3) The Operator shall issue prior notice of three months to the Agency where there shall be electricity service termination.

4) Relevant provisions of laws pertaining to the rights of electricity customers shall be applicable for customers of rural electrification.

## 18. *Integration to National Grid*

The Executive Secretariat shall plan and advise that rural electrification be designed in view of future interconnection to the national grid.

## 19. *Monitoring and Enforcement of Approved Projects*

The Executive Secretariat, may supervise the implementation of approved rural electrification projects and ensure that the projects are executed in accordance with the approved project proposal and take appropriate legal measure pursuant to the project contract.

## 20. *Right of Way and Land Use*

Relevant provisions of the Electricity Proclamation No. 86/1997 dealing with Land Use and Right of Way shall apply to rural electrification projects.

## 21. *Environmental Protection*

Rural Electrification Project plans, construction, operation and maintenance shall respect environmental protection laws.

## 22. *Safety*

1) Operators shall take the necessary precautions to ensure the safety of persons working in the plant, the public and avoid damage to property.

2) Relevant provisions of safety standards and conditions in Electricty Proclamation No. 86/1997 and Electricity Operation Regulations No. 49/1999 shall be applicable for rural electrification standards.

## 23. *Books of Account*

The Executive Secretariat shall keep accurate and complete books of account with supporting documents.

፳፬· አዲት

፩· ለዋናው ኦዲተር በሕግ የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የፈንዱ ሂሣብ ቦርዱ በሚሰይመው የውጭ ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራል።

፪· ሂሣቡ የሚመረመረው በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ባለው የሂሣብ ምርመራ መርሆዎችና ሥርዓት መሠረት ሆኖ የኦዲት ሪፖርቱ ቦርዱና የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር አስተያየት እንዲሰጡበት ይቀርብላቸዋል።

፫· የቴክኒክ ምርመራ ፣ በተመረጡት ተግባራት ላይ በየዓመቱ ይከናወናል።

፳፭· የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም የመተባበር ግዴታ አለበት።

፳፮· ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

፩· ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሊያወጣ ይችላል።

፪· ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን በደንቡ በሚወሰነው መሠረት ሚኒስቴሩ ወይም ቦርዱ ሊያወጡ ይችላሉ።

፳፯· ተፈጻሚ የማይሆኑ ሕጎች

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ በዚህ አዋጅ በተደነገጉት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

፳፰ አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከጥር ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ጥር ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም

ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

24. *Audit*

1) Without prejudice to the powers given by law to the Auditor General, the Books of Acocunt of the Fund shall be audited annually by an external auditor to be appointed by the Board.
2) The Books of Account shall be audited in accordance with internationally acceptable principles and procedures, and the Audit report shall be submitted to the Board and the Ministry of Finance for comments.
3) Technical inspection shall annually be done on selected activities

25. *Duty to Co-operate*

Any individual, Government organs and private organizations shall have the duty to cooperate in the execution of this Proclamation.

26. *Power to Issue Regulations and Directives*

1) The Council of Ministers may issue regulations necessary for the implementation of this Proclamation.
2) The Ministry or the Board, as may be determined by Regulations, may issue directives necessary for the implementation of this Proclamation

27. *Inapplicable Laws*

No law shall, in so far as it is inconsistent with this Proclamation, have effect in respect of matters provided for by this Proclamation.

28. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 6th day of February, 2003.

Done at Addis Ababa, this 6th day of February, 2003.

GIRMA WOLDE GIORGIS
PRESIDENT OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE